# ይህ ወር በታሪክ

በዚህ በያዝነው ወር ረዥም ዕድሜና ታሪክ ያለው የኢትዮጵና የሩስያ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት የተጀመረበት መቶ አስረኛ ዓመት የሚታሰብበትና የሚዘከርበት ነው;;

ከዛሬ መቶ አስር ዓመት በፊት የካቲት 5 1898 ዓ.ም አዲስ አበባ ከጧቱ ሶሰት ጀምሮ ብዛቱ ከስድስት ሺህ ያላነሰ የአፄ ምንሊክ ጦር የዘመቻ ትጥቁን ታጥቆ በተጠንቀቅ የመጀመሪያ የሩሲያ የዲፕሎማቲክ አባላትን ለመቀበል ይጠባበቃል;; የሩስያ የልኡካን ቡድንም ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያለውን የደንከል በረሃ አቋርጦ ተራራና ገደሉን ተጉዞ በዋዜማው የካቲት 4 ከአዲስ አበባ መግቢያ ላይ ሰፍሮ ያደረ ሲሆን ከቀኑ አምስት ሰዓት አካባቢ የስዊድን ዜጋ በሆነው የአፄ ምንሊክ አማካሪ እየተመራ ከከተማው ይገባል;;

ጋሻና ጦሩን ታጥቆ ዝናሩን ጠምጥሞ ለክብር ሰላምታ የተሰለፈውንም ጦር በዝግታ ሰንጥቆ እያለፈ ከንጉሱ መናኸሪያ ሲደርስ የክብር መድፍ ይተኮስለታል;; የልኡካኑ መሪ አምባሳደር ቭላሰቭም ቡድኑን እየመራ ንጉሱ ከተቀመጡበት ዙፋን ቀርቦ እጅ ሲነሳ አፄ ምንሊክ "እንኳን ደህና መጣችሁ የወዳጃችንን አገር የሩስያን መልእክተኞች ስንቀበል ደስታችን ከፍተኛ ነው" [1] ሲሉ ከልባዊ ደስታና ፈገግታ ጋር ይቀበሏቸዋል;; አምባሳደሩም "ግርማዊ ሆይ! የመላው ሩስያ ገዢ ፣ ሀያሉና ገናናው የሩስያ ንጉስ ለክብርነትዎ ልባዊ ሰላምታና የወዳጅነት መልእክት እንዳቀርብ የመጀመሪያው የልኡካን ቡድን መሪ አድርጎ ወደ አገርዎ መርቶኛል;; የልኡካን ቡድኑም የጦር መኮንኖችንና ሀኪሞችን የያዘ የክብር ዘብ ሲሆን ፣ የማይሻረውንና የማይገሰሰውን የታላቁን ንጉስ ፈቃድና ትዕዛዝ በመፈፀም ከአገርዎ ገብቼ እነሆ ለግርማዊነትዎ የክብር ደብዳቤ ሳቀርብ ታላቅ ኩራት ይሰማኛል ..." [2] በማለት ለረዥም ዘመናት የኢትዮጵያ መሪዎች ምኞትና ጥረት የነበረውን የኢትዮጵያና የሩስያን የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ምስረታ እውን ያደርጋል;;

የኢትዮጵያና የሩስያ ግንኙነት የዲፕሎማቲክ ምስረታ ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት ረዥምና ሳቢ ታሪክ ያለው ነው;;

የሩስያ የታሪክ አዋቂዎች እንደሚያወሱት የሁለቱ አገሮች ትውውቅ የተጀመረውና "አብሲኒያ" የሚለው ቃሉ ራሱ በሩስያ ኦፊሲያል መዝገበ-ቃል ውስጥ የገባው በ15ኛው ክፍለ ዘመን ነው;; ሆኖም ከዛ በፊትም ስለ ኢትዮጵያ የሚያወሱ ተባራሪ ወሬዎችና ዜናዎች ሩስያ ይደርሱ እንደነበረ ይነገራል;;

የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከአሌክሳንድርያና ከኢየሩሳሌም ጋር ባላት ግንኙነት አማካኝነትና እንዲሁም ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሩስያ ምእመናንና ቀሳውስት ወደ ቅድሲቱ ምድር ለመሳለም ሲመጡ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በፓሌስታይንና በግብፅ ቆይታቸው ከኢትዮጵያውያን ምእመናን ጋር ለመገናኘት መቻላቸው ስለ ኢትዮጵያ መጠነኛ ግምት እንዲኖራቸው አድርጓል;;

ሆኖም ግን ኢትዮጵያ እንደ ጂኦ-ፖለቲካል ክልልና ራሱን የቻለ መንግስትነት በሩስያ መታወቅ የጀመረው ከ17ኛው ክፍለ ዘመን አሌክሴይ ሚኻይሎቭ ከሚባለው የሩስያ ንጉስ ዘመን ጀምሮ ነበር;; የሩስያ የገዥ መደቦች ስለ ኢትዮጵያ አንጻራዊ የተሟላ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስቻላቸውን እውቀት ያገኙት በወቅቱ የሳክሶን ገዢ የኤርነስት የፖለቲካ አማካሪ ከነበረው ኢዮብ ሉዶልፍ ከሚባል የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂ ሲሆን ይህም ሰው በአውሮፓ ስለ ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረበ ተብሎ የሚነገርለት ነው;; በዚያን ዘመን ሩስያ ከቱርክ ጋር በነበራት ጦርነት ከአውሮፓ አገሮች አጋር ለማግኘትና ፀረ ቱረክ ግንባር ለመፍጠር ጥረት የምታደርግበት ወቅት ሲሆን ለዚህም ዓላማ ከሳክሶን መሳፍንት ጋር ለመነጋገር የተላከው የሩስያ መልእክተኛ ከዚሁ የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂ ጋር ይገናኛል;;

ሉዶልፍም ለሩስያው ንጉስ መልእክተኛ በሩቅ ስለምትገኘው ኢትዮጵያ ማንነትና ታሪክ በማስተዋወቅ ወደ ኢትዮጵያ መልእክት እንዲልክና ፀረ ቱርክ ግንባር ውስጥ ለማስገባት እንዲሞክር ሃሳቡንና ምክሩን ይለግሰዋል;; ሆኖም ግን ለሩስያዊው መልእክተኛ የማያውቁትና እንዲህ ሩቅ የሆነ አፍሪካዊ አጋር በነበረው ሁኔታ ለሩስያ ጠቃሚነቱ አጠራጣሪ በመሆኑ በቸልታ ያልፈዋል;;

ይሁን እንጂ የሁለቱ ሰዎች ግንኙነት የወለደው ትልቁና አብይ ቁም ነገር  የሉዶልፍ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሀፍ ሩስያ መግባትና ስለ ኢትዮጵያ የሰፋና የላቀ አመለካከት እንዲኖር ማስቻሉ ነበር;;

በንጉስ ቀዳማዊ ፒተር (Peter The Great /1676-1718 ዓ.ም/) ዘመን በታሪክና በመልክአ-ምድር ተገልላና ተዘግታ ለዓለም ሁሉ ባዕድ ሆና የቆየችው ሩስያ ለመጀመሪያ ግዜ በዓለም የፖለቲካ መድረክ ላይ እንደ አንድ ታላቅ ሃይል የወጣችበት ግዜ ነበር;; ወጣቱ ንጉስ በደቡብና በሰሜን የሩስያን የባህር በሮች የከፈተና የሩስያን የባህር ሃይል ቆርቁሮ በሰላማዊ (pacific) ውቅያኖስ ላይ የሩስያን የባለቤትነት መብት ያረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ማዳጋስካር ላይ ለመርከቦቹ የባህር መደብ በማቆም ወደ ህንድ የሚያደርስ ቋሚ የባህር መስመር ለማደራጀት ተነሳስቶ እንደነበረ ይነገራል;;

የሩሰያን ኢምፓየር ለማስፋትና በዓለም ላይ ያላትን ተፅዕኖና ለማጎልበት ከሚያደርገው ጥረትና ትግል አኳያ ኢትዮጵያ እንደ ሉዶልፍ መጽሀፍ አገላለፅ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን አገር መሆኗ ብቻ ሳይሆን  በሃይማኖት ቅርበትና  ተመሳሳይነት ከሩስያ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር ያልተቆጠበ ጥረት የምታደርግ መሆኗ የሪፎርማተሩን ንጉስ ትኩረት እንድትስብ አድርጓል;; በአሌክሳንደሪያው ፓትርያርክ አቡነ ኮስማ /1718-1722 ዓ.ም/ አማካይነትም ከኢትዮጵያ መሪዎች ጋር ግንኙነት ለማድረግ ጥረት ያደረገ ሲሆን በዚህም ሳይወሰን ቀጥታ ግንኙነት ለመፍጠር ቋንቋና መንገድ የሚያውቅ የውጭ ዜጋ እንዲያፈላልጉ ለውጭ ቆንስላዎቹ ሁሉ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር;;

ሆኖም ግን ትልሙ ሳይሰምር እሱም ያልፍና ከእሱ በሁዋላ በተከተለው ግዜ  የሩስያ ኢምፓየር እየተዳከመ የውጭ እንቅስቃሴውም እየቀዘቀዘ በመምጣቱ በአፍሪካና በተለይም በኢትዮጵያ ላይ አቅዶት የነበረው ኤክስፒዲሽን እየተረሳ ይቀራል;;

ታላቁ የሩስያ ደራሲና ገጣሚ የአሌክሳንደር ፑሽኪን ኢትዮጵያዊ ቅድመ አያት አብራሃም ጋኒባል በዚህ ግዜ የኖረና ቀዳማዊ ፒተር አሳድጎና አስተምሮ የባህር ሃይሉም ከፍተኛ የጦር መኮንን አድርጎት እንደነበር እዚህ ላይ የሚወሳ ነው;;

ከዚህም በሁዋላ የአሌክሳንድሪያው ፓትርያርክ አቡነ ማቴዎስ /1751-1752 ዓ.ም/ በሁለቱ አገር መሪዎች አገናኝ ለመሆን ሞክረዋል;; በንግስት ኤልዛቤት ፔትሮቭና  ዘመን በ1751 ዓ.ም ከዳግማዊ ኢያሱና ከእናታቸው ንግስት ምንትዋብ የተላኩ ሁለት ደብዳቤዎች በእሳቸው አማካኝነት ሩስያ ይደርሳሉ;; የእነዚህም ደብዳቤዎች መልእክት የእጅ ጥበብ አዋቂዎችና የሃይማኖት መሪዎችን እንዲልኩላቸው የሚጠይቁና እንደ  ሁሌው ከምስራቁ አብያተ-ክርስቲያናት ጋር ለመዋሃድ ያላቸውን ፍላጎት የሚገልጹ ነበሩ;; [3]  ሆኖም ከሩስያ መሪዎች በኩል ምላሽ ሳያገኝ ይቀራል;;

በቀጣዩ አንድ ምዕተ ዓመት ማለትም ከ1751-1855 ዓ.ም ድረስ በነበረው ግዜ ከሁለቱም ወገኖች በኩል ለመቀራረብና ግንኙነት ለመቋጠር የረባ  ጥረት ሳይደረግ ያልፋል;; ይሁን እንጂ በዚህ ሙሉ መቶ ዓመት ግዜ ውስጥ  ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖርም ስለሁለቱ አገሮች የሚያወሱ ዜናዎች በየግዜው ሁለቱም ጋ ይደርሱ ነበር;;

በልዩ ልዩ መንገድ ሩስያ የገቡ የኢትዮጵያ ጥንታዊ  ጽሁፎች  በንጉሱ  የፒተርስቡርግ መጽሃፍት ቤት፣ በየገዳማቱ፣ በሳይንስ አካዳሚ የእስያ ሙዚየምና በኪዬቭ የመንፈሳዊ አካዳሚ ውስጥ በርካታ ስብስቦች ተጠራቅመው ነበር;;

ኢትዮጵያውያንም በዚህ ግዜ ስለ ሩስያ ብዙ ማወቅና መገንዘብ ችለዋል;; ለዚህም ትልቁን አስተዋፅኦ ያበረከቱት አርመኖችና ግሪኮች ነበሩ;; ከቱርኮች ወረራና ጭፍጨፋ (genoside) በሽሽት ከአገራቸው ተሰደውና ፈልሰው በብዛት ኢትዮጵያ የገቡት አርመኖችና ግሪኮች በነገስታቱ ፈቃድ በንግድና በእጅ ጥበብ ስራ ተሰማርተው ከኢትዮጵያውያን ጋር ጎን ለጎን የኖሩ ነበር;;

ይህን በሚመለከት በሁዋላ አፌን (አቴንስ) የሚገኘው የሩስያ ቆንሲል ከጻፋቸው ራፖሮች ባንዱ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል;; "ከጣሊያኖች መምጣት በፊት በበዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰፋሪ ግሪኮች ነበሩ;; የህክምና አዋቂዎች፣ ነጋዴዎች፣ አራጣ አበዳሪዎችና አስተርጓሚዎች በጥቅሉ በአብሲኒያና በሰለጠነው ዓለም መሀከል አገናኝ እነሱ ነበሩ;; ማንኛውም ግንኙነት በሩሰያና በአቢሲንያ መሀከል ይካሄድ የነበረው በግሪኮች አማካይነት ወይም ጌታ ቤተ-መቃብር (ፓሌስታይን) ..በሚገኙት

ኢትዮጵያውያን መነኩሴዎች በኩል ነበር ...ስለ ታላቋ ሩሲያም የሰሙትና በምስራቁም ዓለም ክርስቲያኖች ጋሻና መከታ እንድትሆናቸው ወደ እርሷ ፊታቸውን እንዳዞሩ በአቢሲኒያ የሚያውቁት ከግሪኮች ነው ብሎ መናገር ይቻላል..." [4] ይላል;;

የቁጠራቸው ብዛት ከግሪኮቹ የማይተናነሰው አርመኖችም ሩስያን ለኢትዮጵያውያን በማስተዋወቅ የማይተናነስ ድርሻ አብርክተዋል;; ሩስያ ታላቅ የክርስቲያን አገር እንደሆነችና የክርሰትና ሃይማኖትም ጠባቂና ተከላካይ መሆኗን የሚገልጽ በጎ ዜና በሰፊው ተዳርሶ ነበር;;

በ19ኛው ክ/ዘመን የሁለቱ አገሮች ግንኙነት ሲጀመርም ይህን የመሰለ የመተዋወቅ ቅድመ ሁኔታ የነበረ ሲሆን ጅማሬውም ግልጽ የሆነ ዓላማና ግብ የተንተራሰ ነበር;; ሙሉ መስተጋብር አይኑረው እንጂ ሁለቱ መንግስታትና ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት እኩል የሆነ መሳሳብ ነበራቸው;;

በ19ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ ላይም በቅድሚያ ግንኙነት ለመፍጠር የተሞከረው ከኢትዮጵያ በኩል ነበር;; በ60ኛዎቹ ዓመታት ላይ አፄ ቴዎድሮስ (1855-1868 ዓ.ም) በተደጋጋሚ ለንጉስ ቀዳማዊ ኒኮላይ ፀረ ቱርክ የሆነ ግንባርና ወታደራዊ ህብረት ለመፍጠር የሚያሳስብ መልዕክት መላካቸውን የታሪክ ማስታወሻዎች ይመዘግባሉ;;[5] ግን አንዱም ሩስያ ስለመድረሱ የተጨበጠ መረጃ የለም;;

ወቅቱ ሩስያ የክሬምያ ጦርነት /1853-1856/ በክሬምያ ደሴት ምክንያት ከቱርክ ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ ጋር ጦርነት ላይ የነበረችበት ግዜ ነበር;; ኢትዮጵያውያንም ጦርነቱን ይከታተሉት እንደነበረና አፄ ቴዎድሮስም ለሩስያ ያላቸውን የድጋፍ ስሜት ለመግለጽ የነበራቸውን አንድ ለእናቱ መድፋቸውን 'ሲቫስቶፖል' ብለው በጦርነቱ ታዋቂ በነበረው የክሬምያ ደሴት ዋና ከተማ ስም እንደሰየሙት ይታወሳል;;

አፄ ቴዎድሮስን የተኩት አፄ ዮሀንስም /1872-1889/ ግንኙትን ለመቀጠል ጥረት አድርዋል;; በ1874፣ በ1876ና በ1879 ሶስት ግዜ በተከታታይ ለንጉስ አሌክሳንድር ደብዳቤ ልከው ነበር;; በነገሱ ማግስት ሀምሌ ወር ላይ 1872 ዓ.ም ኢየሩሳሌም በሚገኙት የኢትዮጵያ ገዳም መነኩሴዎች አማካይነት ከሩስያ ቆንስላ ጋር ግንኙነት በማድረግ ስልጣናቸውን ለማጠናከር የሩስያው ንጉስ እንዲደግፏቸውና ቆንስላም በአቢሲኒያ እንዲያስቀምጡ አስጠይቀው ነበር;;[6] ሆኖም የሩስያው ንጉስ " ለንጉስ ዮሀንስ ቆንስላ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ግዜው አልደረሰም ብላችሁ በቃል መልእክት አድርሱ በማለት አዘዋል" [7] ሲል ኢየሩሳሌም ያለው የሩስያ ቆንስላ ዘግቧል;;

የሩስያ መንግስት ታላቅነት ፣ የክርስትና ሃይማኖት ጠባቂና የክርስቲያኖች ሁሉ ጠበቃ መሆኑ በሰፊው መታወቁ እርስ በርስ አንዱ ባንዱ ላይ የበላይነት ለማግኘትና ንጉሰ ነገስት ለመሆን የሚታገሉትን የየክልሉ ንጉሶች ከሩስያ መሪዎች ጋር ግንኙነትና ወዳጅነት ለማበጀት ድጋፍም ለማግኘት በግል እንዲጥሩ አድርጓቸው ነበር;;

በሁዋላ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት የሆኑት የሸዋው ንጉስ ምንሊክ አፄ ዮሀንስን አልፈው ግንኙነት ለመፍጠር ከሞከሩት አንዱ ናቸው;; በ1887 ዓ.ም ኢየሩሳሌም ባሉ መነኩሴዎች በላኩት መልእክት ከሩስያ አቡንና የመንፈሳዊ አገልጋዮች እንዲላክላቸው ጠይቀው ነበር;;[8]

የአፄ ዮሀንስ አልጋ ወራሽ ተብለው ይታሰቡ የነበሩት የሰሜን ኢትዮጵያ ዝነኛ የጦር አዝማች ራስ አሉላ በ1885 ዓ.ም በሩስያና በኢትዮጵያ መሀከል የፖለቲካና የወታደራዊ ግንኙነት እንዲፈጠር የሚሹና " ... ከአፄ ዮሀንስ ህልፈት በሁዋላ ለንጉሰ ነገስትነቱ መንበር ሲበቁ በግል ሩስያ ድረስ በመሄድ ከሩስያ ንጉስ ጋር ለመወዳጀት ያላቸውን ፍላጎት ገልጸው ነበር.."[9] ሲል ኢቫኖቭ የተባለ ሩስያዊ ዘግቧል;;

ይቀጥላል